# የፓልቶክ አርበኛ

የፓል ቶክ አርበኞች ፣ እነ ስም አይጠሬ
ኮምፒዩተር ጫካቸው ፣ ሳይገሉ ጎፈሬ
ከጧት እስከማታ ፣ አሉባልታ ወሬ
በወጣት ተጧሪ ፣ ጉድ ይሰማል ዛሬ።

ሁሉም ጀግና ሆነ ፣ ቤቱ ተቀምጦ
ወይ በረሃ አይገባ ፣ ወይ አይገል አድፍጦ
የሚሰራን መስደብ ፣ አፍን አሞጥሙጦ
አየር ባየር ሆነ ፣ ትግል ተገልብጦ።

የካድሬው አበዛዝ ፣ ያጋሰሱ መንጋ
ወፈፌውም ፣ እብዱም ፣ አይምሮው ያልረጋ
ለከት የለው ላፉ ፣ ለሰው አይሰጥ ዋጋ
መረን በለቀቀ ፣ ምላስ እየወጋ
አውቃለሁ ባይ በዝቶ ፣ አዳማጭ ፍለጋ
መአቱን ያወርዳል ፣ በስድብ አለንጋ
ሲንጫጫ ያረፍዳል ፣ መሽቶ እስከሚነጋ ።

ከሁሉም ከሁሉም ፣ የሚያቅለሸልሸው
በነጋ በጠባ ፣ ሁሌ እሚያቀረሸው
አጃቢ ከዳሚ ፣ መድረክ ያቆሸሸው
የወያኔ ካድሬ ፣ ደርግ ሆኖ የሸሸው
ሙት እየወቀሰ ፣ ሲዘልፍ የሚያመሸው
ባልተገራ ምላስ ፣ አፉን የሚያሟሸው ።

በትግል ሜዳ ላይ ፣ ደሙን ያፈሰሰ
ያገር የወገኑን ፣ ክብር ፣ ያላስገሰሰ
በፓልቶክ አርበኛ ፣ እየተከሰሰ
ሰማዕታት ረከሰው ፣ ባንዳው ተሞገሰ
የፋሽስት የጠባብ ፣ ተግባር ተወደሰ ።

መምጫው ያልታወቀ ፣ እንዳሸን የፈላ
በስድብ ጦርነት ፣ አንገት እየቀላ
ጠርሙሱን ጨብጦ ፣ እየጋፈ አተላ
ወጣት ጡረተኛ ፣ ሰርቶ እንኳ እማይበላ
መድረክ ያጣብባል ፣ ታጋዩን ሲያጥላላ ።

የሚያደማ ቢሆን ፣ የሚያቆስል አፋቸው
እንደወሬው ቢሰምር ፣ እንደ ጭካኔያቸው
ያሰቡት ተሳክቶ ፣ በለስ ቢቀናቸው
ከሳሽ ዳኛ ሆነው ፣ ስልጣን ቢሰጣቸው
በምድረ ኢትዮጵያ ፣ሰውም አይተርፋቸው ።

የባዕድ ቅጥረኛ ፣ ምንደኛ ምስለኔ
የደርግ እርዝራዥ ፣ ካልሆነ ወያኔ
ዘወትር ቀረርቶ ፣ አበባው ዘላኔ
የሞተን መኮነን ፣ አይገባኝም እኔ ።

ወያኔ እያዳፋው ፣ አድርጎት ከርታታ
ታጋዮችን መስደብ ፣ ጠኋትና ማታ
ከኔ በላይ ማለት ፣ በከንቱ ድንፋታ
ወገኑን ሲያጥላላ ፣ ይውላል ሲመታ
ቋጠሮ ያጠብቃል ፣ ችግሩን ላይፈታ ።

ሁሉንም አዋቂ ፣ የፓል ቶኩ አርበኛ
ዲስኩር የሚወደው ፣ የወሬ ሱሰኛ
ተሳድቦ ካልዋለ ፣ እንቅልፍ የማይተኛ
ዘመን አመጣሹ ፣ አዲሱ ጦረኛ
የወያኔ የደርግ ፣ የገንጣይ ቅጥረኛ ።

የፓልቶክ ታጋዮች ፣ እነ ስል  ምላሱ
ገዳይ ሲያወድሱ ፣ ሟች እየወቀሱ
የተገነባውን ፣ ሲንዱ ሲያፈርሱ
አዋቂ በምድር ፣ ማን አለ እንደነሱ  ?

በሸርክት አፉቻእው ፣ ፈጩና ከመሩት
በየመድረካቸው ፣ አቡክተው ጋገሩት
ሁሉን ተቃዋሚ ፣ ፈርጀው መተሩት
እናውቃለን ባዮች ፣ በባዶ የኮሩት
የፓልቶክ አርበኖች ፣ ጥላቻ እሚዘሩት
ወያኔን አይነኩም ፣ አስሬ እሚያጓሩት ።

የፓልቶኩ ጀግና ፣ ቆብ አጥልቆ መጣ
እሳት እንደነካው ፣ ተልባ እየተንጣጣ
ማነው በግዛቴ ፣ ሊጋፋኝ የመጣ
ቡራ ከረዩ አለ ፣ ደነፋ ተቆጣ
ይሄም ስልጣን ሆኖ ፣ ባቅሙ ሲቀጣ
የተቃወመውን ፣ ከክፍል አስወጣ ።

ስራ ፈት ቦዘኔ ፣ አይሰራ አያሰራ
ወይ ጠላት አይባል ፣ ወይ ከታጋይ ጎራ
የታገለ መስሎት ፣ መከራ ሲጠራ
አፉ አለኝ ተብሎ ፣ በባዶ ፉከራ
ኮሽ ሲል ሊደበቅ ፣ በከንቱ ሲያቅራራ
ቃሊቻ ይመስል ፣ ይውላል ሲያጓራ ።

ታዛቢው
July 30/2009